Aug 30,2013

# ለጌታ ሊኖረን የሚገባ በቂ ምላሽ

በ መሀልይ 5፡1-6 ወስጥ ያለችው ተዋናይ ሴት ስለወዷ በቂ እወቀት የነበራት ሴት ብትሆንም ወዷ ሊጎበኛት ሲመጣ

- በቂ ምላሽ ለማስጠት ዘገየች
- አጥጋቢ ምላሽን ባለማስጠቷ ወዷ ጥሏት ሄደ
- ከዚህም የተነሳ የደረሰባትን መከራ እናያለን

ለዚች ባለእድል ሴት የቀረበው ግብዣን መሀ 5፡1 ላይ እናገኘዋለን፡፡እንዲህ ይነበባል፡-

<<እስክትረኪ ድረስ ጠጪ>

ከዚህ አወደ ንባብ የምንረዳው አንድ ነገር አለ፡፡ወዷ ወደ ዚች ሴት የመጣበት ምክንያት ጠጥታ እንድትረካ ነው፡፡በእኛም ህይወት የጌታ ከፍ ያለው ሃሳብ ከእርሱ ጋር ከሚኖረን ህብረት የተነሳ ስለምናገኘው ህብረት እና እርካታ ነው፡፡ይህም እረፍትና እርካታ በህይወታችን ሲኖር ጠንካራና የሚታይ ምስክርነት ይኖረዋል፡፡

እብራውያን 4፡10-11 ላይ <<ስለዚህ ያንን ትውልድ ተቆጥቼ ፡-ዘወትር በልባቸው ይስታሉ መንገዴን ግን አላወቁም አልሁ እንዲሁ ፡-ወደ እረፍቴ አይገቡም ብዬ በቁጣዬ ማልሁ፡፡>>የሚል ቃል ገራሚ ቃል አለ፡፡የጌታችን የልብ ሀሳብ ለህይወታችን መልካም ሆኖ ሳለ ብዙ ጊዜ ልቤ ሲያፈነግጥና፣ሳስቸግረው እና ስንጋደድ እራሴን አገኘዋለሁ፡፡ማለትም የኔ ህይወት ከዚች ሴት ምላሽ ጋር በሚገባ ይመሳሰላል፡፡

ዮሀንስ 10፡10 ላይ እኔ ህይወት እንዲሆናችሁ እንዲበዛላችሁ መጣሁ ይላል፡፡ማለትም ህይወቱ በዝቶልን ለሌሎች እንድንተርፍ ነው የጌታ ዋና የልብ ሀሳብ!

ግን እንደምታዘበው ከኔም ሆነ ከብዙዎች ክርስትያኖች በቂ ምላሽ እያገኘ አይደለም፡፡ብዙ ነገሮችን በቀለም ደረጃ እናውቃለን፡፡ግን መጠየቅ ያለበት ጥያቄ፡-

ጌታን በሚገባ በግል እናውቀዋለን ወይ ?

ህይወቱ በዝቶልናል ወይ ? እረክተናል ወይ ?

ከዚህ የተነሳ ሰዎች በእኛ ህይወት ክርስቶስን እያዩ ነው ወይ ?

እነዚህ ከላይ ያሉት ጥያቄዎች በበቂ ሁኔታ በህይወታችን ምላሽ እንዲያገኙ ወደ ጌታ በሚገባ መቅረብ አለብን ብዬ አምናለሁ፡፡ሀያዋርያው ያእቆብ <<ወደ እግዚአብሄር ቅረቡ እርሱም ይቀርባችኋል>> እንደሚል በእኛ በኩል የምንወስዳቸው የመቅረብ ውሳኔዎችና እውነተኛ ተግባሮች በህይወታችን ትልቅ ፍሬ እንድናፈራ ያደርጉናል፡፡

ወደ ጌታ በቀረብን ቁጥር በመንፈሱ እየታደስንና ከፍ ያሉ እይታዎችን እያገኘንና ግንኙነታችን እየጠለቀ ይመጣል፡፡በዚህ በጠለቀ ግንኙነትም መንፈሳዊ እርካታ ወደ ህይወታችን ይመጣል፡፡ይህ እርካታ ደግሞ ምድራዊና ረብ ለሌላቸው ነገሮች እንዳናጎነብስና እንዳንሰጥ ሀይል ይሆነናል፡፡

የጌታችን ለኛ ያለው አላማ በመሀልይ 5፡1ላይ እንደተጠቀሰው እስክንረካ ድረስ ከመንፈሱ እንድንጠጣ ነው፡፡ለዚህ ቃል ሚጋገጫ የሚሆን ደግሞ ዮሀ 7፡37 ላይ <<ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ፡፡በእኔ የሚያምን መጽሀፍ እንዳለ የህይወት ውሀ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል>>የሚል ድንቅ ግብዣን እናገኛለን፡፡ይህንንም ኢየሱስ የተናገረው ታላቁ የአይሁዶች የዳስ በአል ሊያልቅ ትንሽ ጊዜ ሲቀረው ሲሆን ሰው ሁሉ በግብዣ ተንበሽብሾ ከከረመ በኋላ በሚሆኑ በሌላ መንገድ የቆያችሁበት ግብዣ

ወስጣዊ እና ዘለቄታዊ እርካታ የለውም ማለቱ ይመስላል፡፡አዎ በእርግጠኝነት በየትኛውም ድል ያለ ግብዣ ላይ ብገኝ ወስጣዊ የሆነና ዘለቄታ ያለው እርካታ አናገኝም ለጊዜው ብንሸነገልም፡፡

በዚህ በዮሀንስ ላይ ባለው ቃል ማስረት ምን ይሁን ምን የሰው ልጅ ወስጥ የሆነ <<ጥማት>> እንዳለ ቃሉ ይጠቁመናል፡፡ይህንን <<ጥማት>>ደግሞ በተለያየ ነገር ለሚርካት የሰው ልጅ የሚያደርገው ነገር የለም፡፡ነገር ግን የሰው ልጅ ወደ ነፍሱ እረኛና ጠባቂ በሚገባ ካልተመለሰ በስተቀር በዚህ ምድር ነፍሱን የሚያረካ ከጥማቱና ከመቅበዝበዝ የሚያወጣ የሚያላግለው ምንም ነገር የለም፡፡

ኢሳ 55፡1-2 ላይ <<እናንተ የተጠማችሁ ሁሉ ወደ ወሀ ኑ ገንዘብም የሌላችሁ ኑና ግዙ ብሉም ኑ ያለ ገንዘብም ያለ ዋጋም የወይን ጠጅና ወተት ግዙ፡፡ገንዘብን እንጀራ ላይደለ የደካማችሁንም ዋጋ ለማያጠግብ ለምን ትመዝናላችሁ አድምጡኝ በረከትንም ብሉ ሰውነታችሁም በጮማ ደስ ይበለው>>የሚል ሌላ እጅግ የሚገርም ግብዣን እናገኛለን፡፡በተለያየ ምድራዊ በሆነና ከሰአታት በኋላ በሚበን ደስታ መሳይ ነገር ጊዜያችሁን አታጥፉ ይልቁንም <<ልባችሁ በጮማ ደስ ይበለው>> ነው ቃሉ የሚለን፡፡<<ጮማ>> የሚለው ቃል በዚህ አወድ ማስረት ከእግዚአብሄር ቃልና መንፈስ ጋር ግንኙነታችን ሲጠልቅ የምናገኘውን በረከት ነው የሚወክለው፡፡ሁልጊዜ ይህንን ቃል ሳነብ ከባድ መንፈሳዊ ጉጉትን ይፈጥርብኛልና እወደዋለሁ፡፡ይህ በረከት ደግሞ ልባችንን ከምናስበው በላይ እጅግ ደስ ያሰኘዋል፡፡ደስታው ደግሞ በሰአታት የሚበን ሳይሆን እያደር የሚጨምርና እየበረከተ የሚሄድ ነው፡፡ይህንን በህይወቴ ስላየሁ በቂ ህያው ምስክር ነኝ፡፡ይህ ነው እግዚአብሄር ለእኛ ያለው አላማና ፍቃድ!

ስለዚህ ያለምንም ማመላወልና ማመንታት ወደ ጸጋው ዙፋን መጥተን በፊቱ በቂ ጊዜን በመወሰንና በሚጨፈን እናሳልፍ፡፡ከእግዚአብሄርም ቃል ጋርም በቂ ጊዜ ይኑረን፡፡ያኔ አስደናቂ የሆነ ህይወት ወስጥ እራሳችንን እናገኘዋለን!

## የእግዚአብሄር ጉብኝት(spiritual visitation)

<<Revival >> ወይም <<መነቃቃት>> ማለት የሞተን ነገር ወደ ህይወት መመለስ ማለት ነው፡፡በሌላ በኩል ደግሞ መነቃቃት ማለት ባጭሩ <<እግዚአብሄር መጣ>>ማለት ነው፡፡ትንቢተ እንባቆ3፡3 ላይ<< እግዚአብሄር ከቴማን ቅዱሱም ከፋራን ይመጣል >> ብሎ በወደፊት ጊዜ ግስ ነው የሚገልጸው፡፡በእንግሊዝኛ መጽሀፍ ቅዱሶች ወስጥ ግን "God came…" ብሎ በሀላፊ ጊዜ ነው አረፍተ ነገሩ የሚጀምረው፡፡እንባቆ ምእራፍ ሶስት ላይ ያለውን ቃል በመነቃቃት ዙሪያ የሚጽፉ የእግዚአብሄር ሰዎች ያዘውትሩታል፡፡እዚሁ ምእራፍ ላይ ከቁጥር 4 ጀምሮ <<እግዚአብሄር ሲመጣ>> የሚሆኑ ድንቅ ክስተቶችን እስከ ቁጥር 16 ድረስ በስፋት ይዘረዝራል፡፡እኔ ግን አለፍ አለፍ እያልኩ በግልጽ በሚገባ ሁኔታ የተገለጹትን ለመጥቀስ ልሞክር ፡-

- ቆመ ምድርንም አወካት፤ተመለከተ አህዛብን አናወጠ፤የዘላለም ተራሮች ተቀጠቀጡ፤የዘላለም ኮረብቶች ቀለጡ
- በቃልህ እንደሚልህ መቅሰፍትን አወጣህ ቀስትንም ገተርህ ምድርንም ሰንጥቀህ ፈሳሾችን አወጣህ
- ተራሮች አንተን አይተው ተጨነቁ
- ፍላጾችህ ከወጠፀት ብርሀን የተነሳ ከሚብለጨለጨው ከጦርህ ጸዳል የተነሳ ጸሀይና ጨረቃ በመኖሪያቸው ቆሙ
- በምድር ላይ በመአትህ ተራመድህ አህዛብን በቁጣ አሄደህቸው
- የሀጢያተኛውን ቤት ራስ ቀጠቀጥህ ማሰረቱን እስከ አንገቱ ገለጥህ
- የአለቆችን ራስ በገዛ በትራቸው ወጋህ

ከዚያም እንባቆ እግዚአብሄር እየመጣ እንደሆነ በመንፈሱ ስላወቀ እንዲህ ይላል፡-<<እኔ ሰምቻለሁ ልቤም ደነገጠብኝ ከድምጹ የተነሳ ከንፈሮቼ ተንቀጠቀጡ መንቀጥቀጥ ወደ አጥንቶቼ ወስጥ ገባ በስፍራዬ ሆኜ ተናወጥሁ>>፡፡እግዚአብሄር በክብሩ በሰዎች መሀል ሲገኝ ብዙ ነወጥ እንደሚሆን ከላይ ጀምሮ ያሉት አገላለጾች ያሳዩናል፡፡የእግዚአብሄር መንፈስ በሀይል ወርዶብኝ ከንፈሬ

በሀይል ተንቀጥቅጦና ማናገር አቅቶኝ ያወቃል አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በርከት ያሉ ጊዜያት፡፡ለአገልግሎት መድረክ ላይ ወጥቼ ለተወሰነ ደቂቃ ማስበክ እና ቃል ማውጣት አቅቶኝ ያወቃል፡፡ስለዚህ ይህ አገላለጽ በማጡም ቢሆን ይገባኛል፡፡

መዝ 68፡1-35 ላይም እግዚአብሄር ሲነሳ ወይም ሲገለጥ የሚሆኑ ድንቅ ነገሮች በስፋት ተዘርዝረዋል፡፡ይህ ክፍል ሲጀምር ‹‹እግዚአብሄር ይነሳ›› ብሎ ነው የሚጀምረው፡እግዚአብሄር ሲነሳ እና በክብሩ ሲገኝ የሚሆኑ ነገሮችን አለፍ አለፍ ብዬ እዘረዝራለሁ፡ -

- ጠላቶቹ መገቢያ ነው የሚያጡት፡ -ሰም በእሳት እንደሚቃልጥ ይቀልጣሉ፤ጢስ እንደሚበንን ይበናሉ

- ጻድቃን በእርሱ ፊት ሀሴት ያደርጋሉ በሀይልም ደስ ይላቸዋል
- እስረኞች ከእስራታቸው ይፈታሉ

- ምድር ትናወጣለች ሰማያት ያንጠበጥባሉ(የቃሉንና የመንፈሱ በህዝብ ማህል ማዘነብን ነው የሚያሳየን)

- የደከሙ ይበረታሉ ይጸናሉ

- የጠፉው ቃል ይገኛል(እግዚአብሄር ቃሉን ይሰጣል) ብሉም እንቆቅልሽ ይፈታል

- በቤት የምትኖር ምንም ተሳትፎ ያልነበራት ሴት እንኳን ምርኮ ተካፈለች ይላል(የበረከቱን ሰፊነት ነው የሚያማለክተን)

- ብዙ ሰዎች መንፈሳዊ ስጦታዎችን ይቀበላሉ(የጸጋ ስጦታዎችን)

- ብዙ ሰዎች ከብዙ ጉድ ይድናሉ ይወጣሉም(ከሞት መውጣትም በእግዚአብሄር ነው የሚሆነው ይህንን ያማለክታል)

- ሀይል ያለው ቃል ይለቀቃል
- ብዙ ሰዎች ሀይልንና ብርታትን ይቀበላሉ

እዚህ ላይ ትልቅ ሊስተዋል የሚገባው ነገር የእግዚአብሄርን በጉባኤና በህዝብ መካከል ማለጥ ሰው ሊያቅደውና ሊያደራጀው አይችልም፡፡ሁለት ነገሮች ለዚህ ክስተት ወሳኝ ናቸው፡-

1.የእግዚአብሄር ሉአላዊነት(God’s sovereignity):-ጌታችን ይህንን አይነት ክስተት ነፍሱ በወደደች ሰአት ያደርጋል

2.የሰው ሀላፊነት(man’s responsibility):-ሰው ይህ ክስተት መቼ እንደሚመጣ ባያወቅም በብዙ ናፍቆትና በጋለ ጸሎት ማጠበቅ አለበት

የእግዚአብሄር ጉብኝት ወደ እኛ እንዲመጣ ልንኮተኩታቸው የሚገቡ ነገሮች የሚከተሉት ናቸው፡ -

1.ከልብ የሆነና እውነተኛ መመለስ ያስፈልገናል (2 ዜና 7፡13-15 ያንቡ)፡- ይህንን ሁለተኛ ዜና ላይ ያለውን ቃል አንድ የእግዚአብሄር ሰው እንዲህ ብለውታል፡ -

‹‹the final and finished formula for revival>>

2.መንፈሳዊ ጥማትና ረሀብ (ሉቃ ፡20-21)፡-አንድ ሰው በማነቃቃት ዙሪያ የጻፉት ጽሁፍ ላይ የሚደረሳው ድንቅ ሁለት ነገሮች በልቤ ተጽፈው ቀርተዋል፡፡እነርሱም በእንግሊዝኛ <<fasting and feasting›› ሲሆኑ ጾምና የእግዚአብሄርን ቃል በብዛት መመገብ መንፈሳዊ ጥማትንና ረሀብን ያቀጣጥላሉ ብለው ነው ጽሁፉ ላይ የሚያስገነዝቡት፡፡በግሌ የመንፈስ ረሀቤ ሲቀንስ እነዚህን ሁለት ነገሮች አብዝቼ አደርጋለሁ፡

ዊሊያም ቡዝ የሚባሉ ትልቅ የእግዚአብሄር ሰው አንድ የቤተ ክርስትያን አገልጋይ በቤተ ክርስትያኑ ለወጥ አጥቶ ሲያማክራቸው እንዲህ አሉት፡‹‹try tears›› በአማርኛ ‹‹እስቲ እንባን ሞክር››ነው ያሉት፡፡ይህ አባባል ብዙ በጌታ ፊት በብዙ

እንባና ጩኸት ወስጥ መሆን እንዳለብን ይጠቁመናል፡፡መዝ 14፡2 ላይ <<የሚያስተውል እግዚአብሄርን የሚፈልግ እንዳለ ያይ ዘንድ እግዚአብሄር ከሰማይ የሰው ልጆችን ተመለከተ>>እንደሚል የክብር ጌታ ከአርያም አይቶ እንዲራራና ልቡን ወደ እኛ እንዲያዘነብል ለዚህ ለከበረ ነገር ዋጋ የሚከፍሉና የጸሎት ሚስጥር የገባቸው ሰዎች በዚህ ዘመን በጣም ያስፈልጋሉ፡፡

3>የተሰበረ ልብና መንፈስ(ኢሳ 57፡14-15)፡-እግዚአብሄር የልብ መሰበርንና ትህትናን ስለሚወድ በፊቱ ባዶነታችንና ያለሱ ምንም ማድረግ የማንችል መሆናችንን አውቅና በማስጠት ወስጣችንን ማሳየት መቻል አለብን፡፡መዝ 34፡18 ላይ <<ልባቸው ለተሰበረ እግዚአብሄር ቅርብ ነው>> ስለሚል የልብ መሰበር በህይወታችን እንዲመጣ በፊቱ መወደቅ አለብን፡፡

የእግዚአብሄር ጉብኝት ሲመጣ የሚታዩ ለወጦች ፡-

- ሀይል ይጨምራል
- ቤ/ክ ትጠራለች
- ቅድስና የህይወት መሰረት ይሆናል
- ንጹህ መለኮታዊ ፍቅር በመካከላችን መታየት ይጀምራል
- ቤ/ክ በውጭው አለም ማህበራዊ ተጽእኖን ማምጣት ትጀምራለች

ስለዚህ የእግዚአብሄር ጉብኝትና ሚልካሚዙ እጁ በትወልዳችን መሀል መጥታ ክብሩን እንድናይ ያለማሰለስና ያለመታከት እንጸልይ!

ስሜ በቀለ በላቸው(ዶ/ር) ይባላል በጌትስበርግ ሜሪላንድ ወስጥ ነው የምኖረው፡ጌታን በስነ-ጽሁፍ እና መንፈሳዊ ትምህርቶችን በማስተማር አገለግላለሁ፡በነዚህ አጫጭር መጣጥፎች እና ባለፉት ጽሁፎች ላይ አስተያየት ለማስጠት ለምትፈልጉና አብራችሁኝ የወንጌልን ስራ ለማሰራት ለምትፈልጉ በሚቀጥሉት አደራሻዎች ልታገኙኝ ትችላላችሁ፡-

Email address:beke_abay@yahoo.com

Phone number:240-330-5004

ጌታ ህይወታችሁን ይባርክ!